# <u>መድረኩ ሊጠየቅ ይገባዋል !</u>

**አማኑኤል ዘሰላም**
(amanuelzeselam@gmail.com)

አንድ ድርጅት ሆነ የፖለቲካ ቡድን ሊደገፍም ሆነ ተቃዉሞ ሊደርስበት የሚገባዉ፣ በስልጣን ላይ ሆኖ ባሳየዉ ዉጤት ፣ ስልጣን ገና ያልጨበጠ በተቃዋሚ ጎራ ያለ ከሆነ ደግሞ «ስልጣን ብንይዝ እናከናዉነዋለን» በሚለዉ አጀንዳዎቹና የፖለቲካ መርህዎቹ ነዉ።

በሲያትል የተጀመረዉ የመድረክ አመራር አባላት ኢትዮጵያዉያንን የማነጋገር ተልእኮ ፣ እንደ አትላንታ ደንቬር ባሉ ከተሞችም ቀጥሏል። በአትላንታ አቶ ተመስገን ዘዉዴ እና አቶ ገብሩ አስራት ለኢትዮጵያዉያን በመድረክ እንቅስቃሴ ዙሪያ ንግግር አድርገዋል። በዉጭ አገር የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊም በገንዘብ በሞራል ከመድረኩ ጎን እንዲሰለፍ የልኡካን ቡድኑ ጥሪ አቅርቧል።

«ለምንድን ነዉ መድረክን የምንደገፈው ?» የሚለዉ ጥያቄ መቼም ማንም ለመድረክ ድጋፉን ከመስጠቱ በፊት የሚጠይቀዉ ወይንም ሊጠይቅ የሚገባዉ ነዉ። ኢሕአዴግን ስለምንቃወም ከሆነ መድረክን እንደግፋለን የምንለዉ በጣም ተሳስተናል። ከኢሕአዴግ ጋር ባለተገናኘ መልኩ መድረክ በራሱ ልንፈትነዉና ልንፈትሸው ይገባል።

## <u>መድረኩ ከኢሕአዴግ የሚለይባቸዉ ነጥቦች በጥቂቱ</u>

«መድረኩ ከኢሕአዴግ በምን ይለያል ? መድረኩ ስልጣን ቢይዝ አገር ተረክቦ ማስተዳደር ይችላል ወይ ? መድረኩ እንደ ስብሰብ፣ አሊያም በአባል ድርጅቶቹ ደረጃ ዲሞክራሲያዊ ነዉ ወይ ? » ለሚሉና ለመሳሰሉ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ይጠበቅበታል።

መድረኩ በፖሊሲ ደረጃ ከኢሕአዴግ የሚለያቸው መሰረታዊ ነጥቦች አሉት። በዋናነት ከሚጠቀሱት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡

- በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 39 የሰፈረዉ የመገንጠል መብት እንደማያስፈልጋና ሕገ መንግስቱ በዚህ አንጻር መሻሻል እንዳለበት
- የአሰብ ወደብ የኢትዮጵያ የሚሆንበትን ሁኔታ ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ማመቻቸት
- ከአማርኛ ሌላ በብዙ ሕዝብ የሚነገረን ቋንቋ የፌደራል ቋንቋ (አፋን ኦሮሞ ማለት እንደሚሆን ጥርጥር የለዉ) ከአማርኛ ጋር የፌደራል ቋንቋ እንዲሆን ማድረግ

በአንቀጽ 39 የመገንጠል ጥያቄና እና በአሰብ ጉዳይ ላይ መድረኩ የወሰዳቸው ዉሳኔዎች የሚደገፉ ትክክለኛ የኢትዮጵያ ሕዝብን ፍላጎት ያንጸባረቁ ዉሳኔዎች ናቸዉ።

ከአማርኛ ሌላ አፋን ኦሮሞ የፌደራል ቋንቋ በማድረጉ አንጻር ግን፣ የኢሕአዴግ አቋም የተሻለ አቋም ሳይሆን እንደማይቀር አስባለሁ። አፋን ኦሮሞ የፌዴራል ቋንቋ መሆን አለበት የሚል መከራከሪያ መድረኩ ካቀረበ፣ ሊመልሳቸዉ የሚገባ መሰረታዊ ጥያቄዎች ይኖራሉ። እነርሱም «ለምንድን ነዉ አፋን ኦሮሞ ከሌሎች ቋንቋዎች ተለይቶ የፌደራል ቋንቋ የሚሆንበት ምክንያት ? ትግሪኛ፣ ሶማሌኛ፣ ጉራጌኛ.፣ ወላይትኛስ .. የፌደራል ቋንቋ የማይሆኑበት ምክንያት ምንድን ነዉ ? ይሄስ የእኩልነትን ጥያቄ አይስነሳም ወይ ? ... » የሚሉ ናቸዉ።

ከዚሁ ጋር በተገናኘ መድረኩ ሌላ ሊመልሳቸዉ የሚገባ ጉዳዮች፣ በኦሮሚያ አፋን ኦሮሞ፣ በሶማሌ ሶማሌኛ በትግራይ ትግሪኛ ብቻ የክልሎቹ የሥራ ቋንቋ መሆናቸውን በተመለከተ ነዉ። አፋን ኦሮሞ የፌዴራል ቋንቋ እንዲሆን ከተፈለገ መድረኩ አማርኛ፣ ከአፋን ኦሮሞ፣ ትግሪኛና ሶማሌኛ ጋር በክልሎቹ የሥራ ቋንቋ እንዲሆን ለምን አልተጠየቀም ?

የአፋን ኦሮሞ የፌደራል ቋንቋ እንዲሆን መድረኩ ሲስማም «የትኛዉን ፊደል በፌደራል ደረጃ መጠቀም እንደሚገባ አስቦ ነዉ ወይ ? » የሚል ሌላ ጥያቄም ይነሳል። የዚህ የፊደል ሁኔታ በግልጽ መቀመጥ ያለበት ይመስለኛል። ኢትዮጵያዊ የሆነዉን ግእዝ አሽቀንጥሮ፣ ያለ ሕዝቡ ፍላጎትና ሕዝቡ ሳይጠየቅ በወቅቱ የመንግስት አካል በነበሩ በጥቂት የኦነግ ባለስልጣናት ዉሳኔ፣ በሕዝቡ ላይ የተጫነ፣ ከሮማ የመጣ የላቲን ፊደል፣ የኢትዮጵያ ፌደራል መጻፊያ ይሁን ማለት በአብዛኛዉ፣ ታሪኩንና ቅርሱ በሚወደው ኢትዮጵያዊ ዘንድ ችግር አያስከትልም ወይ ?

ኢሕአዴግ ከምርጫ 2002 በፊት አፋን ኦሮሞ በግእዝ ፊደል እንዲጻፍና በዚያም ትምህርት እንዲሰጥ አስቦ እንደነበረ ለገዢው ፓርቲ ቅርበት ያላቸዉ ወገኖች ገልጸዉልኝ ነበር። እነዚህ ወገኖች ሲናገሩ «በትግራይ ተማሪዎች ትግሪኛ ሲማሩ፣ አማርኛም መጻፍና ማንበብ ይማራሉ፤ ፊደሉ ግእዝ ስለሆነ። ብዙ የትግራይ ተማሪዎች አማርኛም ትግሪኛ አውቀዉ ነዉ የሚወጡት። በኦሮሚያ ግን ብዙዎች አማርኛ ማንበብና መጻፍ አይችሉም። አፋን ኦሮሞ በግእዝ ፊደል ቢሆን ኖሮ ግን፣ የፌደራል ቋንቋ የሆነዉን አማርኛ በቀላሉ መማር ይችሉ ነበር።» የሚል ምክንያት ነበር የሰጡኝ።

እንግዲህ ኢሕአዴግ የአገራችን ኢትዮጵያ ዉርስና ቅርጽ የሆነዉ የግእዝ ፊደልን ሊያስፋፋ ባሰበበት ወቅት፣ መድረኩ የላቲን ፊደል የፌደራል ቋንቋ መጻፊያ እንዲሆን አጀንዳዉ አድርጎ የሚንቀሳቀስ ከሆነ፣ አንድ በአሉታዊነት ከኢሕአዴግ የሚለይበት ትልቅ ነገር ተገኘ ማለት ነዉ።

## <u>መድረኩና አሁን ያለዉ በቋንቋ ላይ ብቻ ተመሰረተ የተባለዉ ፌዴራል አወቃቀር</u>

አቶ ገብሩ አስራት መድረኩ በአትላንታ ባደረገዉ ስብሰባ ግልጽ እንዳደረጉት፣ መድረኩ በፌደራል አወቃቀር ዙሪያ ገና ስምምነት አልደረሰም። የመድረክ አባል የሆነዉ የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ አሁን ያለዉ ፌደራል አወቃቀር መቀየር እንዳለበት በፐሮግራሙ ግልጽ አድርጓል። ነገር ግን አሁን ያለዉን በቋንቋ ላይ ብቻ የተመሰረተ ፌደራል አወቃቀር የሚደግፉ ፣ የፌደራል አወቃቀሩ ቋንቋ፣ ጂኦግራፊን፣ ኢኮኖሚን፣ የሕዝቡን አሰፋፈርና የሕዝቡን ፍላጎት ከግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ አዲስ ፌደራል አወቃቀር መኖሩን የሚቃወሙ የመድረክ አባል ድርጅቶች አሉ።

**እነዚህ የመድረክ አባል ድርጅቶች እነማን እንደሆኑ በግልጽ መታወቅ ያለበት ይመስለኛል።** ከዚያም በኋላ በፌደራል አወቃቀር ዙሪያ ኢሕአዴግ ካለዉ፣ ያልተለየ አቋም ለምን እንደያዙ፣ እንዲደግፉቸው ለሚፈልገዉ ሕዝብ ማስረዳት አለባቸዉ።

ለምሳሌ አሁን ባለዉ ፌደራል አወቃቀር የሃረሬ ክልል የሚባል አለ። በዚህ ክልል ሃረሬ/አደሬዎች ወደ 15858 ይደርሳሉ(8.65%) ። ኦሮሞ ነን የሚሉ 103421 ( 56.41%) ናቸዉ። አማርኛ ተናጋሪዎች ደግሞ በሃረር የሃረሬዎችን ሶስት እጥፍ ናቸዉ - 41755 (22.77 %)።

በሃረሬ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 6 መሰረት፣ ሃረሬና አፋን ኦሮሞ የሥራ ቅንቋ ሲሆን አማርኛ የሥራ ቋንቅ እንዳይሆን ተደርጓል። 8% የሚሆነዉ በቋንቋ የመናገርና የመስራት መብት ሲሰጠዉ 23% የሚሆነው አማርኛ ተናጋሪዉ መብቱ ተረግጧል። ለምን ? ይሄ ፍትሃዊ ነዉ ወይ ? ይሄ ጸረ-ዴሞክራሲያዊነት አይደለም ወይ?

በሃረሬ ክልል በሕገ መንግስት አንቀጽ 49 መሰረት፣ የሃረሬ ክልል የስልጣን አካል የሆነዉ 36 አባላት ያሉት የሃረሬ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት ነዉ። ይህ ምክር ቤት ሁለት ክፍሎች አሉት። እነርሱም ከሕዝቡ በነዋሪዉ ብዛት ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚመረጥ የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤና፣ 8% ከሚሆኑት ሃረሬዎች ብቻ የሚመረጠዉ የሃረሬ ብሄራዊ ጉባዔ ነዉ።

በሃረሬ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 59 መሰረት የክልሉን አስተዳዳሪ ፕሬዘዳናት የሚጠቁሙት ስምንት በመቶ ነዋሪዎችን የሚወክለዉ የሃረሬ ብሄራዊ ምክር ቤት ነዉ። የክልሉ ፕሬዘዳንት በ92 በመቶ በሚሆኑ ነዋሪዎች የተመረጠ ሳይሆን በ8 በመቶዎቹ ብቻ የተመረጠ ነዉ። በሌላ አባባል በደቡብ አፍሪካ ጥቂት ነጮች ከተቀረዉ ጥቁር ሕዝብ 3፣ 4፣ 5 እጥፍ መብት እንደነበራቸው፣ በሃረሬ ክልልም ተመሳሳይ ሁኔታ ነዉ ያለዉ።

እንግዲህ አሁን ያለዉን የፌደራል አወቃቀር የሚደግፉ የመድረክ አባል ድርጅቶች አመራር አባላት፣ ይህ አይነቱን አድሎአዊ፣ ኢፍትሃዊና ኢዴክራሲያዊ አወቃቀር እንዴት ያዩታል ? ይህ አይነቱን አወቃቀር ነዉን እንዲቀጥል የሚፈልጉት ?

የሃረሬ ብሄረሰብ ከ16 ሺህ ያነሰ ነዉ። ለነርሱ አንድ ክልል ተሰጥቷቸዋል። ሲዳማዎች 2966474 ይደርሳሉ። የሃረሬዎችን 186 እጥፍ ማለት ነዉ። ጉራጌዎች የሃረሬዎች 110 እጥፍ ናቸዉ። ወላያታዎች 10 እጥፍ ናቸዉ ። ሃዲያዎች 80 እጥፍ ናቸዉ። ጋሞዎች 69 እጥፍ ናቸዉ። ግን እነዚህ ሁሉ ብሄር ብሄረሰቦች የራሳቸዉ ክልል የላቸዉም። ሁሉም በአንድ ላይ ተጨፍልቀዉ የደቡብ ሕዝቦች ተብለዋል።

በሰሜን ጎንደር ያሉ በወልቃይት ጠገዴ፣ በሁመራ የሚኖሩትን «ትግሬዎች ናቸው ካልን» የትግሬዎች ቁጥር በትግራይ 4 ሚሊዮን አካባቢ ይደርሳል። ሰሜን ጎንደር ያሉት «ትግሬዎች አይደሉም ካልን ደግሞ» ትግሬዎች በትግራይ 3.5 ሚሊዮን አካባቢ ይሆናሉ ማለት ነዉ። ትግሬዎች ከሲዳማዎች በ500 ሺህ ብቻ ይበልጣሉ ማለት ነዉ።

ታዲያ ሲዳማዉ ፣ ወላይታዉ፣ ጉራጌዉ ከአፋሩና ከሃረሬዉ፣ ከትግሬዉና ከሶማሌው በምን ይለያል ? ለነርሱስ የራሳቸው ክልል ለምን አይኖራቸዉም ? «ሕገ መንግስቱና አሁን ያለዉ ፌደራል አወቃቀር ትክክለኛና ፍትሃዊ ነዉ። አሁን እንዳለዉ መቀጠል አለበት» ያሉት አንዳንድ የመድረክ አባል ድርጅቶች፣ ታዲያ የራሳቸው ክልል ላልተሰጣቸው ምን ምላሽ ነዉ የሚሰጡት ?

«የብሄር ብሄረሰቦች መብት በትክክል ያለ አድልዎ ይከበር» ካልን እንግዲህ ከሰማኒያ በላይ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች እንደመኖራቸው አገሪቷን በሰማኒያ፣ ዘጠና መሸንሸን ይኖርባታል። ያ ደግሞ የማይቻል መሆኑ የማይቀበል ሰው ይኖራል ብዬ አላስብም።

## የቡድን መብት እና የግልሰብ መብት

ኢሕአዴግ አዲስ አበባ እንደተቆጣጠረ አቶ መለስ ዜናዊ ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም፣ ዶር መኮንን ቢሻዉ፣ ዶር እንድሪያስ እሸቴ ጋር የቴሌቭዥን ክርክር አድርገዉ ነበር። በዚያ ክርክር ወቅት ዶር እንድርያስ አንድ በጣም ቁልፍ የሆነ ሃሳብ አቅርበዉ ነበር። የብሄር ብሄረሰብ መብትን ማረጋገጡ እንደተጠበቀ፣ በብሄር ብሄረሰብ መብት ስም የግለሰብ ሰብአዊ መብቶች መረገጥ የለባቸው ነበር ያሉት። ዶር እንድርያስ ሲያክሉ ሁለቱ መብቶች በሚጋጩበት ጊዜ የቱ ቅድሚያ እንደሚሰጠዉ በግልጽ መቀመጥ እንዳለበት ነበር ያኔ የተከራከሩት።

ብዙ የኢሕአዴግ ደጋፊዎች ሁለቱ መብቶች ሊጋጩ አይችሉም ብለዉ ይከራከራሉ። ነገር ግን ሁለቱ መብቶች ሲጋጩ፣ የግልሰብ መብት ተረግጦ የብሄር ብሄረሰብ መብት ሲከበር አይተናል።

ለምሳሌ የኦሮሚያን ክልል ማየት እንችላለን። በሕገ መንግስቱ መሰረት የኦሮሚያ ክልል የፈለገዉን አይነት የሚተዳደርበትን ሕግ ማዉጣት ይችላል። አሁን ያለዉ የኦሮሞያ ሕገ መንግስት አሁን ባለዉ የፌደራል ሕገ መንግስት መሰረት ሕገ ወጥ ሊባል አይችልም።

ኦሮሚያ እንደ አዲስ አበባ/ፊንፊኔ፣ ናዝሬት/አዳማ ፣ ጂማ የመሳሰሉ በብዛት አማርኛ ተናጋሪዎች የበዙባቸው ቦታዎችን አጠቃላላች(አዲስ አበባ ልዩ አስተዳደር ቢሰጣትም በሕገ መንግስቱ መሰረት እንደ ኦሮሚያ አካል ተደርጋ ነዉ የምትቆጠረዉ።)

የኦሮሚያ ሕገ መንግስት አንቀጽ 5 መሰረት አፋን ኦሮሞ የሥራ ቋንቋ ሲሆን የሚጻፈዉም በላቲን ነዉ። የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 33 ደግሞ በክልሉ ዉስጥ ነዋሪ የሆነና የክልሉን የሥራ ቋንቋ የሚያውቅ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በማንናዉም የክልሉ መንግስታዊ ወይም ህዝባዊ ሥራ ተመርጦ ወይም ተቀጥሮ የመስራት መብት አለው ይላል። **ይህ ማለት በኦሮሚያ፣ አፋን ኦሮሞ የማያውቅ ኢትዮጵያዊ በክልሉ ላሉ ማናቸዉም ሃላፊነቶች ሊመረጥ ሊሰራ አይችልም፣ በክልሉ መስሪያ ቤቶች አይቀጠርም ማለት ነዉ። የጠባብነት ፖለቲካ ይሉታል ይሄ ነዉ።**

ከአምስት አመታት በፊት የተደረገዉ የሕዝብ ቆጠራ የአዲስ አበባን እና የአማርኛ ተናጋሪዎች ቁጥር በእጅጉ አሳንሷል። እንደዚያም ሆኖም ግን አዲስ አበባን ጨምሮ በኦሮሚያ የሚኖሩ እራሳቸዉን «ኦሮሞ አይደለንም» የሚሉ ኢትዮጵያዉያን ወደ 20 በመቶ ይጠጋሉ። የነዚህ 20% የሚሆኑ ኢትዮጵያዉያን በሚፈልጉት ቋንቋ የመናገር፣ የመማር፣ ለክልሉ እንደ ዜጋ የመመረጥ መብታቸዉ በሕግ ተነፍጓል። የግለሰብ ሰብአዊ መብታቸው በብሄር ብሄረሰብ መብት ስም ታፍኖ፣ በአገራቸዉና ባደጉበት መንደር እንደ ሁለተኛ ዜጋ እየተቆጠሩ ነዉ።

ይሄ የሆነበት ዋና ምክንያት፣ በግልጽ የብሄር ብሄረሰብም ሆነ ማናቸዉም የቡድን መብት፣ የግለሰብ ሰብዓዊ መብቶች ባልደፈረ መልኩ እንደሚከበር ግልጽ ባለመደረጉ ነዉ።

እንግዲህ መድረኩ በዚህም ቁልፍ ጉዳይ ላይ ያስቀመጠዉ ነገር የለም። ለብሄር ብሄረሰብ መብቶች መቆሙ፣ የብሄር በሄረሰቦችን ጉዳይ በኃላ መልኩ ማራመዱ ባልከፋ ነበር ። ነገር ግን በብሄር መብት ስም የግለሰብ መብት መረገጥ እንደሌለበት፣ ሁለቱ መብቶች ከተቃረኑ ለየትኛዉ ቅድሚያ እንደሚሰጥ ግልጽ ማድረግ ያለበት ይመስለኛል።

በኢትዮጵያ አገር የማስተዳደር ብቃትና ችሎታ እንዲኖረኝ እየሰራሁ ነዉ የሚለዉ መድረክ፣ በነዚህ በሌሎች ቁልፍና መሰረታዊ በሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄዎች ላይ የጠራ አቋም መያዝ ካልቻለ፣ ዜጎች ስለ መድረኩ የፖለቲካ አቋም የበለጠ በተረዱ ቁጥር ችግር ያጋጥመዋል።

ኢሕአዴግ የዘር አደረጃጀትን ትቶ ሕብረ ብሄራዊ ለመሆን እየሰራ ነው። ኢትዮጵያዉያንን አንድ የሚያደርጉ ሰፋፊ ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም እየተንቀሳቀሰ ነዉ። በዉጭ ግንኙነት ዘርፍ ኢትዮጵያ በአካባቢዋና በአፍሪካ በአጠቃላይ ትልቅ ቦታ እንድትደርስ እያደረገ ነው። የሰንደቅ አላማ ቀን በማክበር ከጊዜ ወደ ጊዜ ኢትዮጵያዊነትን እና አንድነት እያጠናከረ ነዉ። ከላይ እንደጠቀስኩት የኢትዮጵያ ቅርስ የሆነዉ ግእዝ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች መጻፊያ እንዲሆን እቅድ ሊኖረዉ እንደሚችልን ይነገራል። መድረኩ መርሳት የሌለበት የአሁኑ ኢሕአዴግ የ1997 ኢሕአዴግ አይደለም። ስለዚህ ተቃዋሚ ስለሆኑ ብቻ ድጋፍ እናገኛለን ካሉ በጣም ተሳስተዋል። እንዲደገፉ ከፈለጉ የተሻሉ መሆናቸውን ማሳየት አለባቸዉ።

በነገራችን ላይ አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝን እና አቶ ደመቀን ጨምሮ ኢሕአዴግ መተካካት በሚለዉ መርህዎቹ በርካታ ወጣቶችን ወደ አደባባይ አውጥቷል። በመድረኩ የምናያቸው አመራር አባላቶች ጥንት የነበሩ አመራር አባላቶች ናቸዉ። ዶር በየነ፣ ዶር መራራ፣ ዶር ነጋሶ፣ አቶ ተመስገን፣ አቶ አሥራት ጣሴ የመሳሰሉ የመድረክ አመራር አባላት፣ የአቶ ቡልቻ ደመቅሳ መርህ ተከትለው፣ የመድረክ አመራር በወጣቶችና በአዲሱ ትዉልድ እንዲያዝ አለማድረጋቸው የስብስቡን ደካማነት የሚያሳይ ነዉ። በዚህም ምክንይታ አዲስ አመራሮችን ካለማየታቸው የተነሳ መድረክን ለመደገፍ ፍቃደኛ የማይሆኑ እጅግ በጣም ብዙ ናቸዉ።

እንግዲህ መድረኩ ጊዜ ሳይፈጅ የቤት ስራዉን መስራት ያለበት ይመስለኛል። የተዋሃዳ፣ መሰረታዉ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አንድ አቋም የያዘ፣ በወጣት አመራሮች የሚመራ መድረክን ማየት እንፈልጋለን።

http://chilot.files.wordpress.com/2012/02/oromia-national-regional-state-constitution.pdf
http://chilot.files.wordpress.com/2012/02/harari-regional-state-constitution.pdf
http://www.csa.gov.et/pdf/Cen2007_firstdraft.pdf